**የተማሪዎች እገዳ/መባረር**

የአሌክሳንደሪያ ከተማ የሕዝብ ት/ቤት ቦርድ በተቻለ መንገድ ከእገዳ ይልቅ ሌላ አማራጭ እርምጃ ያበረታታል። እና ወደ መባረር ሊያደርስ የሚችል ባህሪ ለመቀየር አስፈላጊ ድጋፍ ይሰጣል። ኤሲፒኤስ ባለብዙ ደረጃ የድጋፎች ሥርዓት(MTSS)ይጠቀማል የመልሶ ማቆቆም(ሪስቶራቲቪ ፕራክቲስ) ጭምር የያዘ የጥሩ ባህሪ ጣልቃ ገብነት አሰራር ይጠቀማል። ነገር ግን የተማሪዎችንና የሰራተኞችን ደህንነት ለማስጠበቅ ሲባል አንዳንድ ጊዜ የደንብ መተላለፉ መጠን እገዳን ወይም መባረርን ሊያስከትል ይችላል። ስለ ባለብዙ ደረጃ የድጋፎች ሥርዓት(MTSS) በየደረጃ ሊወሰዱ ስለሚችሉ እርምጃዎች ዓይነት ተጨማሪ መረጃዎች በተማሪዎች ባህሪ ደንብ ላይ ይገኛል።

## I. ትርጉሞች

በዚህ ፖሊሲ በአገልግሎት ላይ እንደዋለው፣

**"አማራጭ የትምህርት ፕሮግራም"** በእነዚህ ብቻ ባይገደብም የሚከተሉትን ያካትታል፤ የማታ ትምህርት፣ የአዋቂዎች ትምህርት፣ መደበኛው የትምህርት ፕሮግራም ለእነሱ አግባብነት የሌለው መሆኑ ሲገመት ሌላ በተለይ የተዘጋጀ የትምህርት ፕሮግራም ያካትታል።

**"አፍራሺ ወይም ፈንጂ መሣሪያ"** ማለት (1) ማንኛውም ፈንጂ፣ ተኳሽ ወይም የመርዝ ጋዝ፣ ቦንብ፣ የእጅ ቦንብ፣ ሮኬት ከሦስት አውንስ በላይ መለኮሻ መተኳሻ ያለው ተቀጣጠይ ወይም ተመሳሳይ መሣሪያ፤(2) ማንኛውም መሳሪያ የማደኛ ጠበንጃ ወይም የማደኛ ጠበንጃ ቀለህ በአጠቃላይ ለአደን ስፖርት በተለይ እንደሚውል የሚታመንበት በማንኛውም ስም የሚታወቅ በቀላሉ በሚቀጣጠል ፈንጂ የሚወረወር ወይም ሌላ ኋይል እና የመተኮሻ ቀዳዳ ከግማሽ ኢንች በላይ ስፋት መጠን ያለው እና (3) በማንኛውም መንገድ የተሰራ ወይም ማንኛውንም መሳሪያ ወደ ጎጂ መሳሪያ የሚቀየር ወይም ጎጂ መሳሪያ በቀላሉ መገጣጠም የሚችል ማለት ነው። ጎጂ መሣሪያ ማንኛውንም መሳሪያ ለጦር መሳሪያነት ወይም ለጦር መሳሪያ ዲዛይን እንደገና ያልተሰራን ወይም ማንኛውም ለጦር መሳሪያነት አስቀድሞ ያልተዘጋጀ እና እንደገና ዲዛይን ያልተደረገ እንደ ምልክት መስጫ ፣ የችቦ ማብሪያ (ፖይሮቴኒክ) ፣ መስመር ማሳያ፣ የደህንነት ወይም ተመሳሳይ መሳሪያን አይጨምርም።

**"የሚበጠብጥ ተግባር/ባህሪ"** ማለት ማንኛውም ተግባር የትምህርት ቤት እንቅስቃሴ ሥራዎች እና ሂደቶች እንዲቆረጥ የሚያደርግ ወይም ለተማሪዎች እና ለሌሎችም ጤንነትና ደህንነትና አደጋ የሚያስከትል ወይም የሚረብሽ ወይም የማስተማር ሂደቱን የሚያደናቅፍ ነው።

**"ማግለል"** ማለት የትምህርት ቤት ቦርድ የተባረረ ወይም በቨርጂኒያ ወይም ሌላ ስቴት ከሠላሣ ቀናት በላይ በሌላ ትምህርት ቤት ቦርድ ወይም የግል ትምህርት ቤት ለረዥም ጊዜ የታገደ ተማሪን በትምህርት እንዳይገባ መከልከል ማለት ነው።

**"መባረር"** ማለት በትምህርት ቤት ቦርድ የተወሰደ ማንኛውም የሥነ ሥርዓት እርምጃ በትምህርት ቤት አስተዳደሩ(ዲቪዥኑ) ተማሪው ትምህርት እንዳይከታተል ፈቃድ የተከለከለ እና ከተባረረ በኋላ ለ365 ቀናት ተመልሶ ለመግባት እጩ ያልሆነ ነው።

**"ጠበንጃ"** ማለት በቨርጂኒያ ሕግ አንቀፅ § 18.2-308.1 ወይም (1) መሰረት በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ወይም በትምህርት ቤቱ ኋላፊነት በሚካሄዱ እንቅስቃሴዎች አካባቢ የተከለከለ ማንኛውም መሳሪያ የውድድር ማስጀመሪያ ጠበንጃ፣ የአየር ግፊት(ኑዮማቲክ) ጠበንጃ (ቀለም የሚረጭ፣ ቢቢ፣ አየር የሚረጭ) ነጠላ ወይም ብዙ ተወርዋሪ ነገሮችን ሊተፉ የሚችል ተቀጣጣይነት ያላቸው ንጥረ ነገሮች በማፈንዳት ወይም የአየር ግፊት ሃይል በመፍጠር ፤(2) የዚህ ማቀፊያ ወይም ዓይነት መቀበያ መሳሪያ ፤ (3) ማንኛውም የጠበንጃ ድምፅ ማፈኛ ወይም ድምፅ መቀነሻ ፤ (4) ማንኛውም አጥፊ ማሳሪያ ወይም (5) ጥይቅ ያልጎረሰ በመያዣ ያለ የጦር መሳሪያ ነው።

**"የረዝም ጊዜ እገዳ"** ማለት ማንኛውም የዲሲፕሊን እርምጃ ከ11 እስከ 45 ቀናት ድረስ ተማሪው ትምህርት እንዳይከታተል የተከለለ ነው። የረዝም ጊዜ እገዳ ከ45 ቀናት በላይ ማራዘም ነገር ግን ከ364 በላይ እንዳይበልጥ ሊደረግ ይችላል (i.) በቨርጂኒያ ሕግ አንቀፅ §§ 22.1-277.07 ወይም 22.1-277.08 የተዘረዘረውን ጥፋት ወይም የከፋ የአካል ጉዳት ወይም (ii.) በቨርጂኒያ የትምህርት ዲፖርትሜንት አገላለፅ መሰረት የትምህርት ቤት ቦርዱ ወይም ዋና ሥራ አስኪያጁ(ሱፐርኢንቴደንቱ) ወይም ተወካዩ የሚያባብስ ሁኔታ እንዳለ ከተመለከቱ ።

**"አንድ ዓመት"** ማለት በፌደራል ደንቦች መሰረት 365 ቀናት ነው።

**"የትምህርት ቤት ንብረት"** ማለት ማንኛውም ቋሚ ንብረት ወይም በትምህርት ቤት ቦርዱ በኪራይ ወይም በትምህርት ቤቱ ቦርድ ወይም በቦርዱ ስም በስራ የዋለ ማለት ነው።

**"የአጭር ጊዜ እገዳ"** ማለት ማንኛውም የዲሲፕሊን እርምጃ ከአስር የትምህርት ቀናት ላልበለጠ ጊዜ ተማሪው ትምህርት እንዳይከታተል የተከለለ ነው።

**"የዋና ሥራ አስኪያጁ(ሱፐርኢንቴደንቱ) ተወካይ"** ማለት የሰለጠነ አቤቱታ የሚሰማ ወይም ባለሙያ ሰራተኛ በትምህርት ቤት አስተዳዳር(ዲቪዝኑ) የአስተዳደር ቢሮ ውስጥ ያለ በቀጥታ ለዋና ሥራ አስኪያጁ(ሱፐርኢንቴደንቱ) ወይም ለተወካዮ ተጠሪ የሆነ እና በትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኝ የአስተዳደር ወይም ትምህርት አሰጣጥ ተሳታፊ ያልሆነ ሰራተኛ ነው ።

## II. አጠቃላይ የተማሪዎች እገዳ እና ማባረር

ተማሪዎች በበቂ ምክንያት በትምህርት ቤት ትምህርት እንዳይካታተሉ ሊታገዱ ወይም ሊባረሩ ይችላሉ። ነገር ግን በማንኛውም ሁኔታ ለእገዳ በቂ ምክንያት ማለት ከትምህርት ቤት መቅረት ብቻ ሊሆን አይችልም። **እገዳ ወይም መባረር የሚያስከትሉ ባህሪ ምሳሌዎች በደንብ JGD-R/JGE-R እና የተማሪዎች ሥነሥርዓት ደንብ በዝርዝር ተገልፃል።**

በቨርጂኒያ ሕግ አንቀፅ § 22.1-277 ወይም በቨርጂኒያ ሕግ አንቀፅ §§ 22.1-277.07 ወይም 22.1-277.08 ከተጠቀሰው በስተቀር ማንኛውም ተማሪ ከመዋእለ ሕጻናት እስከ ሦስተኛ ክፍል ድረስ ያለ ተማሪ በአንድ ክስተት ከሦስት (3) ቀናት በላይ መታገድ ወይም ትምህርት እንዳይከታተል ማባረር አይፈቀድም ጥፋቱ (i) የአካል ጉዳት ወይም ሊታመን የሚችል በሌሎች ላይ የአካል ጉዳት የሚፈጠር ስጋት እስካልሆነ ድረስ ወይም (ii) በቨርጂኒያ የትምህርት ዲፖርትሜንት አገላለፅ መሰረት የትምህርት ቤት ቦርዱ ወይም ዋና ሥራ አስኪያጁ(ሱፐርኢንቴደንቱ) የሚያባብስ ሁኔታ እንዳለ እስካልተመለከተ ድረስ።

ማንኛውንም ተማሪ የሚመለከት ሪፖርት ለዋና ሥራ አስኪያጁ(ሱፐርኢንቴደንቱ) የደረሰው በቨርጂኒያ ሕግ አንቀፅ § 16.1-305.1 መሰረት የደንብ መተላለፍ ወይም ጥፋተኛነት ውሳኔ ከተረጋገጠ ትምህርት እንዳይከታተል መታገድ ወይም መባረር ይችላል።

አንዳንድ ረብሻ በሚፈጠረበት ሁኔታ ተማሪዎችን ከክፍል ለማስወጣት የአስተማሪ ሥልጣን ይህን ፖሊሲ አፈፃፀም የሚነካ አይሆንም።

# III. የአጭር ጊዜ እገዳ

## A. አጠቃላይ

አንድ ተማሪ ከአስር (10) ቀናት ላልበለጠ ጊዜ በትምህርት ቤት ዳይሬክተር ወይም በሚመለከተው የአስተዳደር ኃላፊ ሊታገድ ይችላል። የትምህርት ቤት ዳይሬክተር ወይም የሚመለከተው የአስተዳደር ኃላፊ ተማሪውን ሊያግድ ይችላል በቅድሚያ የቃል ወይም የፅሑፍ ማስጠንቀቂያ በእርሱ/እርሶ ላይ የቀረበውን ትሬታ ካሳወቀ በሆላ እና እርሱ/እርሶ ድርጊቱን እንዳልፈፀመ/ች ካሳወቁ የሁኔታው ዝርዝር መግለጫ በትምህርት ቤት ሰራተኛ የሚታወቅ ከሆነ እና ስለተፈጠረው ጉዳይ የእርሱን/የእርሶን ሃሳብ ለማቅረብ እድል ካገኘ/ካገኘች።

አንድ ተማሪ በሚታገድበት ወቅት ርዕሰ መምህሩ ወይም እገዳው በሚመለከት ሃላፊነት ያለበት የሚመለከተው የአስተዳደር ኃላፊ ስለ ጉዳዮ ምንነት ለዋና ሥራ አስኪያጁ(ሱፐር ኢንቴንደንቱ) ወይም ለተወካዮ እና ለወላጅ/አሳዳጊ የፅሁፍ ሪፖርት ያቀርባል።

ማንኛውም የቃል ወይም የፅሁፍ ማስታወሻ ከአስር ቀናት(10) በላይ ላልበለጠ ጊዜ የታገደው ተማሪው ወላጅ/አሳዳጊ እገዳው የሚቆይበትን ጊዜ መጠን፣ የኮሚዪነቲ ላይ የተመሰረተ ትምህርት ፕሮግራም ስለሚገኝበት ሁኔታ፣ አማራጭ የትምህርት ፕሮግራሞች ወይም ሌላ የትምህርት እድሎች እና የእገዳው ጊዜ እንዳለቀ የተማሪውን ወደ መደበኛ ትምህርት ለመመለስ ስላለው ሙብት መረጃዎች ማካተት ይኖርበታል። በትምህርት ቤት አስተዳደሩ(ዲቪዝኑ) የሚሰጠው የኮሚዪነቲ ላይ የተመሰረተ ትምህርት ፕሮግራም ወይም አማራጭ ፕሮግራም ወይም ወይም የትምህርት እድል የሚጠይቀውን ወጪ የሚሸፈነው በወላጅ/አሳዳጊ ይሆናል።.

ትምህርት ቤቱ በሚያካሂደው ምርመራ ወቅት አዲስ መረጃ ከተገኘ የፅሑፍ ማስታወቂያው ሊሻሻል ይችላል እንዲሁም የሚወሰደው የሥነ ሥርዓት እርምጃም ሊቀየር ይችላል።

## B. የአጭር ጊዜ እገዳ አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜ ፤

1. የአጭር ጊዜ እገዳ አቤቱታውን በቀጥታ ተማሪውን ላገደው የትምህርት ቤቱ ርእሰ መምህር ማቅረብ ይቻላል። የእገዳው ማስታወቂያ ብዙውን ጊዜ ከአስተዳደር ኃላፊው በስልክ የሚገለፅ ከዚያም ደብዳቤ የሚከተል ሲሆን ይህ በደረሰው 24 ሰዓታት ውስጥ የአቤቱታ ደብዳቤ በፖስታ፣ በኢሜል ወይም ለትምህርት ቤቱ በአካል በመቅረብ ይኖርበታል።

2. ተማሪውን ያገደው የትምህርት ቤቱ አስተዳዳሪ አቤቱታውን ካልተቀበለው አቤቱታውን በመቀጠል ለርእሰ መምህሩ ማቅረብ ይቻላል። የአቤቱታ ደብዳቤ በፖስታ፣ በኢሜል ወይም ለትምህርት ቤቱ በአካል ልጁን ያገደው አስተዳዳሪ መልስ በተሰጠ በሁለት(2) ቀናት ውስጥ መቅረብ ይኖርበታል።

3. ርእሰ መምህሩ አቤቱታውን ካልተቀበለው የርእሰ መምህሩ ውሳኔ ከደረሰ ባሉት ሦስት(3) የትምህርት ቀናት ውስጥ ከዚያም በቀጥታ ለተማሪዎች አገልግሎት ሥራአስፈፃሚ ዳይሬክተር ማቅረብ ይቻላል።

4. የተማሪዎች አገልግሎት ሥራ አስፈፃሚ ዳይሬክተር አቤቱታውን ካልተቀበለው የመጨረሻው አቤቱታ የተማሪዎች አገልግሎት ሥራ አስፈፃሚ ዳይሬክተር ውሳኔውን ከሰጠበት በአምስት(5) የስራ ቀናት ውስጥ ለዋና ሥራ አስኪያጁ መቅረብ ይኖርበታል። አቤቱታ የፅሁፍ ደብዳቤ በተማሪው የክፍል ደረጃ ለሚመለከተው ዳይሬክተር አማካኝነት መቅረብ ይኖርበታል።

   የዋና ሥራ አስኪያጅ(ሱፐር ኢንቴንደንት) ጽ/ቤት
   ይድረስ ፤ የአንደኛ ደረጃ ወይም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ሥራ አስፈጻሚ ዳይሬክተር
   የአሌክሳንደሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች
   1340 Braddock Place, 4th Floor
   Alexandria, Virginia 22314

ጉዳዩ በሚመለከታቸው አካላት አቤቱታው እንደቀረበ የዋና ሥራ አስኪያጅ(ሱፐር ኢንቴንደንት) ወይም ተወካዩ በአፋጣኝ በርእሰ መምህሩና ወይም በምክትል ርእሰ መምህሩ የተወሰደውን እርምጃ ይመለከታል እና የተማሪውን ባህሪ የሚያሳየውን ማህደር በመመርመር እገዳውን ያፅድቃል ወይም ያነሳል።

የዋና ሥራ አስኪያጅ(ሱፐር ኢንቴንደንት) ውሳኔ የመጨረሻው እንደሆነና ከዚያ አልፎ አቤቱታ ለትምህርት ቤቱ ቦርድ የማቅረብ እድል እንደማይኖር ወላጆች/አሳዳጊዎች እንዲያውቁት መደረግ ይኖርበታል።

## IV. የረዝም ጊዜ እገዳ

አንድ ተማሪ ከ11 እስከ 45 ቀናት ሊታገድ ይችላል የታሰበውን እርምጃ እና ምክንያቱን እና አቤቱታ ለዋና ሥራ አስኪያጁ (ሱፐር ኢንቴንደንት) የማቅረብ መብቱን የሚገልፅ የፅሁፍ ደብዳቤ ለተማሪው እና ለወላጅ/አሳዳጊ ከተሰጠ በኋላ።

ከ11 እስከ 45 ቀናት የሚቆየው እገዳ የሚገልፀው የፅሁፍ ደብዳቤ እገዳው የሚቆይበትን ጊዜ እና በማህበረሰቡ ውስጥ የሚገኘው የትምህርት፣ አማራጭ የትምህርት ፕሮግራም ወይም የጣልቃ ገብነት ፕሮግራም ጭምር እንዲያካትት ይደረጋል። የዚህ ዓይነቱ ማስታወቂያ በተጨማሪ እገዳው ጊዜ እንዳለቀ ተማሪው ወደ መደበኛ ትምህርት የመመለስ እድል እንደሚኖረው ወይም በእገዳው ወቅት ወይም እገዳው እንደተጠናቀቀ ተገቢነት ያለው በትምህርት ቤት ቦርድ የፀደቀ አማራጭ የትምህርት ፕሮግራም መከታተል እንደሚችል ይገልፃል። አስር ቀናት በላይ እገዳ ለሚቆይ ኤሲፒኤስ ለተማሪው የትምህርት እና የድጋፍ አገልግሎት ይሰጣል። የእያንዳንዱ ተማሪ ፕሮግራም አገልግሎት በዋና ሥራ አስኪያጁ (ሱፐር ኢንቴንደንት) ወይም ተወካዩ ይወሰናል። እና በእነዚህ ብቻ ባይወሰነም የሚከተሉትን ያካትታል ፤ በኦንላይን የማስተማሪያ መንገድ ፣ በቤት ውስጥ ማስተማር፣ (ወይም በሌላ ቦታ ትምህርት በመስጠት) እና ከባህሪው ጋር የተገናኘ የማህበራዊ/ የስሜት ድጋፍ መስጠት። በትምህርት ቤት አስተዳደሩ(ዲቪዝኑ) ከሚሰጠው የመደበኛ ትምህርት ፕሮግራም ውጪ የሆነውን በኮሚዩኒቲ ላይ የተመሰረተ ትምህርት ፕሮግራም ወይም አማራጭ ፕሮግራም ወይም የጣልቃ ገብነት ፕሮግራም በእርሱ/በእርሶ እገዳ ወቅት ተማሪው የሚከታተለው/የምትከታተለው የሚጠየቀውን ወጪ የሚሸፈነው በወላጅ/አሳዳጊ ይሆናል።.

የረዝም ጊዜ እገዳ ከ45 ቀናት በላይ ሊራዘም ይችላል ነገር ግን ከ364 ቀናት በላይ መብለጥ አይኖርበትም (I) ጥፋቱ በቨርጂኒያ ሕግ አንቀፅ §§ 22.1-277.07 ወይም 22.1-277.08 ላይ የተገለፀው ከሆነ ወይም የከፋ የሰውነት አካል ጉዳት የሚመለከት ከሆነ ወይም (II) በቪርጅኒያ የትምህርት ዲፖርትሜንት በተገለፀው መሰረት የትምህርት ቤቱ ቦርድ ወይም ዋና ሥራ አስኪያጁ ወይም ተወካዮ የሚያባብስ ሁኔታ መኖሩን ከተመለከተ።

የዋና ሥራ አስኪያጁ(ሱፐር ኢንቴንደንት) ውሳኔ የሚመለከት አቤቱታ የዋና ሥራ አስኪያጁ(ሱፐር ኢንቴንደንት) ውሳኔ በደረሰው በአምስት ቀናት ውስጥ ለትምህርት ቤቱ ሙሉ ቦርድ ማቅረብ ይቻላል። አቤቱታው በትምህርት ቤት ቦርዱ ጥያቄው በቀረበ በ30 ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት።

በዚህ ሰነድ ያለው ምንም ነገር የትምህርት ቤት ቦርዱ ከዚህ ክፍል ጋር በተያያዘ የታገደን ተማሪ በእገዳው ጊዜ ውስጥ አማራጭ የትምህርት ፕሮግራም እንዲከታተል ለመፍቀድ የሚያግደው ነገር እንዳለ ተደርጎ መቆጠር አይኖርበትም።

ትምህርት ቤቱ በሚያካሂደው ምርመራ ወቅት አዲስ መረጃ ከተገኘ የፅሑፍ ማስታወቂያው ሊሻሻል ይችላል እንዲሁም የሚወሰደው የሥነ ሥርዓት እርምጃም ሊቀየር ይችላል።

## V. ማባረር

## A. አጠቃላይ

ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ሊባረሩ ይችላሉ የታሰበውን እርምጃ እና ምክንያቱን እና አቤቱታ ለትምህርት ቤት ቦርዱ የማቅረብ መብቱን የሚገልፅ የፅሁፍ ደብዳቤ ለተማሪው እና ለወላጅ/አሳዳጊ ከተሰጠ በኋላ። የማብራሪያ ማስታወቂያው በደረሰው አምስት(5) ቀናት ውስጥ አቤቱታ ለሙሉ የትምህርት ቤቱ ቦርድ ማቅረብ ይቻላል። አቤቱታ በትምህርት ቤት ቦርዱ በ30 ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት። ተማሪው ያለውን አቤቱታ የማቅረብ መብት ተጠቀመበትም አልተጠቀመበትም የትምህርት ቤቱ ቦርድ የቀረበውን የማባረር ሃሳብ ማፅደቅ ወይም እንዲነሳ ማድረግ ይኖርበታል።

ማንኛውም ለተማሪው እና ለወላጅ/አሳዳጊ የተሰጠው የፅሁፍ ማስታወሻ እገዳው የሚቆይበትን ጊዜ መጠን፣ በኮሚዩኒቲ ላይ የተመሰረተ ትምህርት፣ ሥልጠና ፕሮግራም ስለሚገኝበት ሁኔታ ፣ አማራጭ የትምህርት ፕሮግራሞች ወይም ሌላ የጣልቃ ገብነት ፕሮግራም መረጃ መስጠት ይኖርበታል። ማስታወቂያው በተጨማሪ ተማሪው የእገዳው ጊዜ እንዳለቀ የተማሪውን ወደ መደበኛ ትምህርት ለመመለስ እጩ ስለመሆኑ ወይም በትምህርት ቤት ቦርዱ የፀደቀ ሌላ አማራጭ የትምህርት ፕሮግራም ወይም በትምህርት ቤት አስተዳደሩ ለአዋቂዎች የተዘጋጀውን ትምህርት ፕሮግራም በእገዳው ወቅት ወይም ከእገዳው በኋላ ለመከታተል እና ትምህርት እንደገና በምን ሁኔታ ሊከታተል እንደሚችል መረጃዎች ማካተት ይኖርበታል። በትምህርት ቤት አስተዳደሩ(ዲቪዝኑ) ከሚሰጠው የመደበኛ ትምህርት ፕሮግራም ውጪ የሆነውን በኮሚዩኒቲ ላይ የተመሰረተ ትምህርት ፕሮግራም ወይም ሥልጠና ወይም ወይም የጥልቃ ገብነት ፕሮግራም በእርሱ/በእርሶ እገዳ ወቅት ተማሪው የሚከታተለው/የምትከታተለው የሚጠይቀውን ወጪ የሚሸፈነው ወላጅ/አሳዳጊ ይሆናል።.

በዚህ ሰነድ ያለው ምንም ነገር የትምህርት ቤት ቦርዱ ከዚህ ፖሊሲ ጋር በተያያዘ የተባረረውን ተማሪ በተባረረበት ጊዜ ውስጥ አማራጭ የትምህርት ፕሮግራም እንዲከታተል ለመፍቀድ ወይም ለመጠየቅ የሚያግደው ነገር እንዳለ ተደርጎ መቆጠር አይኖርበትም።

የትምህርት ቤት ቦርዱ ተማሪው በተባረረበት ጊዜ ውስጥ ወደ መደበኛ የትምህርት ክፍል ለመመለስ ፣ አማራጭ የትምህርት ፕሮግራም ወይም በትምህርት ቤት አስተዳደሩ የሚሰጠውን የአዋቂዎች ትምህርት ፕሮግራም ለመከታተል ብቁ አይደለም ብሎ ከወሰነ የፅሁፍ ማስታወቂያው የዚህ ዓይነት ተማሪ ወላጆች/አሳዳጊዎች ተማሪው ከተባረረበት አንድ(1) ቀን ውስጥ ወደ ትምህርት ቤት መመለስ እንዲችል ለትምህርት ቤቱ ቦርድ አቤቱታ ማቅረብ እንደሚችል እና መመለስ የሚችል ከሆነ የሚመለስባቸውን ሁኔታዎች የሚገልፅ ይሆናል።

**ደንብ JGD-R/JGE-R የአሰራር ሂደት እና የቅደም ተከተል የመሰረተ ሲሆን በዚህም መሰረት እንደዚህ ያሉ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት ለመመለስ ማመልከት እና እንደገና በድጋሚ ማመልከት ይችላሉ።** የዚህ ዓይነት መርሃግብር የተቀረጸው ወደ ትምህርት ቤት ለመመለስ የመጀመሪያ ማመልከቻ በትምህርት ቤቱ ቦርድ ወይም በዋና ሥራ አስኪያጁ የሚታይ መሆኑን እና ተቀባይነት ካገኘ ተማሪው ወደ ትምህርት ቤት ከተባረረበት በአንድ ዓመት በሆላ መመለስ ይችላል። ዋና ሥራ አስኪያጁ አቤቱታውን ካልተቀበለው የዚህ ዓይነት መከልከል የትምህርት ቤቱ ቦርድ እንዲመለከተው አቤቱታ ማቅረብ ይችላል።

## B. ወደ መባረር የሚያደርስ ባህሪ

ለመባረር የሚያበቁ ተግባራት ከታች ከተጠቀሱት ሁኔታዎች ውጪ የሚከተሉትን ነጥቦች ባገናዘቡ መልኩ ይሆናል፤

- የባህሪው ዓይነት እና ሁኔታው
- በትምህርት ቤት ማህበረሰቡ ላይ የፈጠረው የአደጋ መጠን
- የተማሪው የዲሲፕሊን ታሪክ፣ ከዚህ ቀደም የፈፃማቸው የደንብ ጥሰቶች ዓይነት እና ብዛት ጭምር
- አማራጭ የትምህርት ምደባ ወይም ፕሮግራም ተገቢነት እና መገኘት
- የተማሪው እድሜ እና የክፍል ደረጃ
- የአእምሮ ጤና፣ የአደገኛ እፅ አጠቃቀም ወይም የልዮ ትምህርት ግምገማ ውጤቶች
- የተማሪው ትምህርት የመከታተል ታሪክ እና የአካዳሚ ውጤት ማህደር እና
- ሌሎች አስፈላጊ ጉዳዮች

እነዚህ ጉዳዮች ባለመታየታቸው ምክንያት በማድረግ የተማሪው መባረር ላይ የተሰጠን ውሳኔ ማጠፍ አይቻልም። በዚህ ንዑስ ክፍል ያሉ የትምህርት ቤት ቦርዱን ከዚህ በታች ስለመባረር በሚመለከት ስለሚደረገው ውይይት ለመወያየት “ልዩ ሁኔታዎች” በሚል የተጠቀሱትን ጉዳዮች ከግንዛቤ ከማስገባት የሚያግደው የለም።

## C. ጠበንጃዎች

የትምህርት ቤት ቦርድ ከትምህርት ቤት ከአንድ (1) ዓመት ላላነሰ ጊዜ ማባረር ይችላል ማንኛውም ተማሪ ጠበንጃ ወደ ትምህርት ቤት ንብረት፣ በቨርጂኒያ ሕግ አንቀጽ §18.2-308.1 መሰረት በትምህርት ቤት ኋላፊነት ስር እንቅስቃሴ በሚካሄድ ቦታ ጠበንጃ ይዞ መጥቶል ብሎ የትምህርት ቤት ቦርዱ ከወሰነ ወይም በዚህ ፖሊሲ በተሰጠው ትርጉም መሰረት ወይም በትምህርት ቤት ንብረት ወይም በትምህርት ቤት ኋላፊነት ስር እንቅስቃሴ በሚካሄድ ቦታ ፔንት ቦል፣ የአየር ጠበንጃ ወይም ቢቢ ጠበንጃ አምጥቶል ብሎ ከወሰነ። የትምህርት ቤት አስተዳዳሪ በትምህርት ቦርድ ፖሊሲ መሰረት ወይም የትምህርት ቤት ቦርዱ ልዮ ሁኔታዎች የሚያሳዮ እውነታዎችን እንዳሉ ተመልክቶ እንደየአግባቡ ምንም የዲሲፕሊን እርምጃ አለመውሰድ ወይም ሌላ የዲሲፕሊን እርምጃ ወይም ሌላ የማባረር እርምጃ ሊወስድ ይችላል። የትምህርት ቤት ቦርዱ ልዮ ሁኔታዎች የሚባሉት ምን እንደሆኑ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል። በተጨማሪም የትምህርት ቤት ቦርድ ደንብ በማውጣት ከማባረር ሌላ ዓይነት የዲሲፕሊን እርምጃ መውሰድ የሚቻል ስለመሆኑ በእነዚህ ዓይነት ጉዳዮች ቅድሚያ ምርመራ እንዲደረግ ለዋና ሥራ አስኪያጁ ወይም ለተወካዮ ሥልጣን ሊሰጥ ይችላል። ልዮ ሁኔታዎች የሚያሳዮ እውነታዎችን ቢኖርም እንኳ በዚህ ሰነድ ያለው ሁኔታ የተማሪውን መባረረ የሚጠይቅ እንደሆነ ተደርጎ መቆጠር አይኖርበትም።

### D. የአደገኛ እፅ ጥፋቶች

ማንኛውንም ተማሪ ወደ ትምህርት ቤት የተከለከለ የአደገኛ እፅ፣ የተከለከለ የአደገኛ እፅ የሚመስል ወይም በቨርጂኒያ ሕግ አንቀፅ §18.2-247 መሰረት ማሪዋና ሃሺሽ ወደ ትምህርት ቤት ንብረት ወይም ትምህርት ቤቱ ኋላፊነት እንቅስቃሴ በሚደረግበት ቦታ ይዞ መጥቶል ብሎ የትምህርት ቤት ቦርዱ ከወሰነ የትምህርት ቤት ቦርዱ ከትምህርት የማባረር ውሳኔ ሊወስን ይችላል። ሆኖም ግን የትምህርት ቤት ቦርዱ ልዮ ሁኔታዎች የሚያሳዮ እውነታዎችን እንዳሉ ተመልክቶ እንደየአግባቡ ሌላ የዲሲፕሊን እርምጃ ሊወስድ ይችላል። በተጨማሪም ዋና ሥራ አስኪያጁ ወይም ተወካዩ ከማባረር ሌላ ተገቢ የሆነ የዲሲፕሊን እርምጃ መውሰድ የሚቻል ስለመሆኑ ለመወሰን በእነዚህ ዓይነት ጉዳዮች ቅድሚያ ምርመራ ያደርጋል። ልዮ ሁኔታዎች የሚያሳዮ እውነታዎችን ቢኖርም እንኳ በዚህ ሰነድ ያለው ሁኔታ የተማሪውን መባረረ የሚጠይቅ እንደሆነ ተደርጎ መቆጠር አይኖርበትም።

## VI. የረዝም ጊዜ እገዳ እና ማባረር በሚመለከት የትምህርት ቤት ቦርድ አቤቱታ ማዳመጥ

የረዝም ጊዜ እገዳ እና ማባረር በሚመለከት የትምህርት ቤት ቦርድ አቤቱታ ማዳመጥ አሰራር እንደሚከተለው ነው።

**A.** የትምህርት ቤት ቦርዱ አቤቱታ በማዳመጥ ሂደቱ ጉዳዮ በቀጥታ በማይመለከታቸው ሰዋች አስፈላጊነት ላይ ይወስናል። የትምህርት ቤት ቦርዱ በተለይ ካልተወሰነ በስተቀር አቤቱታ የመስማቱ ሂደት ለሌላ ወገን ዝግ ይሆናል።

**B.** የትምህርት ቤት ቦርዱ የመከፈቻ ንግግር ከርእሰ መምህሩ ወይም ከእርሱ/እርሶ ተወካይ እና ከተማሪው ወይም ከእርሱ/ከእርሶ ወላጅ(ዋች) /ከአሳዳጊ (ዋች) (ወይም ከእነርሱ ተወካይ) እና በትምህርት ቤት ቦርዱ ፈቃደኝነት ላይ ተመስርቶ የማጠቃላያ ሃሳብ ለማቅረብ ሊፈቅድ ይችላል።

**C.** ከዚያም ሁሉም ወገኖች ማስረጃቸውን ሊያቀርቡ ይችላሉ። ርእሰ መምህሩ ዋነኛ የማስረጃ ሰነድ የማቅረብ ልዮ ኋላፊነት ስላለበት እርሱ/እርሶ ያለውን ማስረጃ በቅድሚያ ያቀርባል። ምስክሮች በትምህርት ቤት ቦርዱ አባላት እና በሁለቱም ወገኖች ሊጠየቁ ይችላሉ።(ወይም በእነርሱ ተወካዮች) የትምህርት ቤቱ ቦርድ በራሱ እንደአስፋላጊነቱ አሰራር ሊቀያይር ይችላል ሆኖም ግን ለሁለቱም ወገኖች ያላቸውን እቃዋች ወይም ተዛማጅ የሆኑ ማስረጃዋች ለማቅረብ ሙሉ እድል እና ሁሉም ወገኖች የመስቀለኛ ጥያቄዋችን የማቅረብ እድል እንዲያገኙ ያደርጋል። ነገር ግን የትምህርት ቤት ቦርድ የተማሪዋችን የምስክርነት ቃል ባለጉዳዮ ተማሪ ወይም የእርሱ/የእርሶ ወላጆች ወይም የእነሱ ተወካዮች በሌሉበት መውሰድ ይችላል የትምህርት ቤት ቦርድ የተማሪ ምስክሮች ደህንነት ለመጠበቅ የዚህ ዓይነት

እርምጃ መውሰድ ተገቢ መሆኑን ካመነበት።

**D.** የትምህርት ቤት ቦርድ ያመነበትን ተጨማሪ ማስረጃ ሁለቱም ወገኖች ማቅረብ ይኖርባቸዋል። የትምህርት ቤት ቦርዱ የማስረጃው አግባብነት እና ጠቃሚነት በሚመለከት ወሳኝ ነው።

**E.** በሁለቱም ወገኖች የሚቀርቡ ማስረጃ ኤግዝቢሽኖች በትምህርት ቤት ቦርድ ተቀባይነት ሊያገኝ ይችላል እና ተቀባይነት ካገኘ ተመዝግቦ የጉዳዮ ማህደር አካል እንዲሆን ይደረጋል።

**F.** የትምህርት ቤት ቦርድ የቀረበውን ሃሳብ በአብላጫ ድምፅ መቀጠል፣ መጣል ወይም መቀየር ይችላል። ነገር ግን መቀየር ለተጨማሪ ጊዜ እገዳን ሊያስከትል አይችልም።

**G.** የትምህርት ቤት ቦርድ ውሳኔውን ከነምክንያቶች ጭምር ለተማሪው፣ የእርሱ/የእርሶ ወላጅ(ዋች)/አሳዳጊ(ዋች) ፣ ለርእሰ መምህሩ እና ለዋና ሥራ አስኪያጁ (ሱፐር ኢንቴንደንቱ) ማስተላለፍ ይኖርበታል።

## VII. አማራጭ የትምህርት ፕሮግራም

የትምህርት ቤት ቦርዱ ማንኛውንም ተማሪ (1) የቨርጂኒያ ሕግ በመተላለፍ የተጠየቀ ወይም የትምህርት ቤት ቦርድ ፖሊሲዎችን በመጣስ በመሳሪያ ፣ አልኮል ፣ በሌላ ሰው ላይ ሆን ብሎ ጉዳት በማስከተል ወይም በቨርጅኒያ ሕግ አንቀድ §16.1-260.G መሰረት ለዋና ሥራ አስኪያጁ ሊገለፅ የሚገባው ጥፋት ዓይነት (2) ጥፋተኛ ከሆነ ወይም በቨርጅኒያ ሕግ በመሳሪያ ፣ አልኮል ፣ወይም በሌላ ሰው ላይ ሆን ብሎ ጉዳት ያስከተለ ወይም በሌሎች ላይ ሊያስከትል ይችል የነበረ ወይም በቨርጅኒያ ሕግ አንቀድ §16.1-260.G መሰረት ለዋና ሥራ አስኪያጁ ሊገለፅ የሚገባው ጥፋት ዓይነት(3) የባሳ ጥፋት ፈጽሞ ከተገኘ ወይም የትምህርት ቤት ቦርድ ፖሊሲን በመተላለፍ ተደጋጋሚ ጥፋቶችን ከፈፀመ (4) በቨርጅኒያ ሕግ አንቀድ 22.1-277.05 መሰረት ከታገደ ወይም (5) በቨርጅኒያ ሕግ አንቀድ 22.1-277.06 መሰረት ከታገደ 22.1-277.07 ወይም 22.1-277.08 መሰረት ወይም በቨርጅኒያ ሕግ አንቀድ § 22.1-277 ንዑስ ክፍል C አማራጭ የትምህርት ፕሮግራም መከታተል ይችላል ። የትምህርት ቤት ቦርድ እንደዚህ ዓይነት ተማሪ ወንጀሉ የተፈፀመበት ቦታ ሳይወስነው እንደዚህ ዓይነት ፕሮግራም እንዲከታተል ሊጠይቅ ይችላል። ማንኛውም ተማሪ አደገኛ እፅ ወይም አልኮል መጠጥ ወስዶ ወይም በእጁ ይዞ በትምህርት ቤት አውቶብስ፣ ንብረት ፣ ወይም ትምህርት ቤቱ በኃላፊነት በሚያካሂደው እንቅስቃሴ ላይ የትምህርት ቤቱ ደንብ በመተላለፍ ከተገኘ የአደገኛ እፅ ወይም የአልኮል መጠጥ ያለአግባብ መጠቀም ምርመራ ወይም ሁለቱንም እንዲያደርግ የትምህርት ቤት ቦርዱ ሊጠየቅ ይችላል። በመርማሪው ሃሳብ ከቀረበ እና በተማሪው ወላጅ/ አሳዳጊ ስምምነት ከተገኘ በህክምና ፕሮግራም እንዲሳተፍ ሊጠይቅ ይችላል።

በተመሳሳይ ትምህርት ቤት ይህ ተማሪ ሌላ አማራጭ የትምህርት ፕሮግራም የሚከታተል ስለመሆን ውሳኔ ለመስጠት በመጠባበቅ ላይ ባለበት ሁኔታበ ቨርጅኒያ ሕግ ህግ አንቀድ § 22.1277.04 መሰረት ሆን ብሎ በሌላ ተማሪ ላይ ጉዳት በሚያስከትለው ተማሪው ላይ በህግ አንቀድ § § 16.1-260.G ርእሰ መምህሩ(ወይም የእርሱ/የእርሶ ተወካይ) የአጭር ጊዜ እገዳ ሊወስን ይችላል ።

እዚህ ላይ እንደተገለፀው “ ተከሶል” ማለት ክስ ወይም ዋራንት ፋይል ተከፍቶል ወይም በተማሪው ላይ ክስ ቀርቦል ማለት ነው።

## VIII. ሪፖርት ማድረግ

**A.** በፌደራል ሕግ፣ ደንብ ወይም ህግጋት በሌላ አባባል ካልተገለፀ በስተቀር ሁሉም ዓይነት የሚከተሉትን የያዙ ክስተቶች ለርእሰ መምህሩ ወይም ለተወካዮ ሪፖርት ይደረጋል፤

1. የአካል ጉዳት ለማድረስ መዛት ወይም የአካል ጉዳት ዛቻና ጥቃት ማድረስ፣ የአካል ጉዳት ሳያስከትል በማንኛውም ሰው ላይ በትምህርት ቤት አውቶብስ ላይ ፣ በትምህርት ቤት ንብረት ግቢ ፣ ወይም በትምህርት ቤት ኋላፊነት በሚካሄድ እንቅስቃሴ ውስጥ እያለ

2. የአካል ጉዳት ዛቻና ጥቃት ማድረስ፣ የአካል ጉዳት ያስከተለ፣ የወሲብ ጥቃት፣ ሞት፣ ተኩስ ፣ በጩቤ መውጋት፣ መቁረጥ ወይም ማንኛውንም ሰው ማቁሰል ፣ በቨርጅኒያ ሕግ አንቀድ § 18.2-47 ወይም በቨርጅኒያ ሕግ አንቀድ § 18.2-48 መሰረት ማንኛውንም ሰው ማፈን ወይም በቨርጅኒያ ሕግ አንቀድ §18.260.3 በተገለፀው መሰረት ማንኛውንም ሰው በትምህርት ቤት አውቶብስ ላይ ፣ በትምህርት ቤት ንብረት ግቢ ፣ ወይም በትምህርት ቤት ኋላፊነት በሚካሄድ እንቅስቃሴ ውስጥ እያለ ያለአግባብ መከታተል፣

3. ከአልኮል፣ ማሪዋና ሃሺሽ ፣ ቁጥጥር የሚደረግባቸው አደገኛ እፃችን ወይም አናቦሊክ ስትሮይድ በትምህርት ቤት አውቶብስ ላይ ፣ በትምህርት ቤት ንብረት ግቢ ፣ ወይም በትምህርት ቤት ኋላፊነት በሚካሄድ እንቅስቃሴ ውስጥ እያለ እንዲሁም ለተማሪ ሕክምና የትዛዝ መድሃኒት መስረቅን ወይም ለመስረቅ መሞከር፣

4. በትምህርት ቤት አውቶብስ ላይ፣ በትምህርት ቤት ንብረት ግቢ ፣ ወይም በትምህርት ቤት ኋላፊነት በሚካሄድ እንቅስቃሴ ውስጥ እያለ የትምህርት ቤት ሰራተኞችን ማስፈራራት፣

5. በቨርጅኒያ ሕግ አንቀድ § 2.1-277.07 ትርጉም መሰረት በትምህርት ቤት ንብረት ግቢ ሕገወጥ ጠበንጃ መሳሪያ መያዝ፣

6. በቨርጅኒያ ሕግ አንቀድ § 18.2-85 መሰረት ሕገ ወጥ ድርጊት ፋየር ቦንብ፣ ፈንጂ ነገሮች ወይም መሳሪያዋች ወይም የውሸት የፈንጂ መሳሪያ ፣ ወይም በቨርጅኒያ ሕግ አንቀድ § 18.2-87.1 መሰረት ፈንጂ ወይም ተቀጣጣይ መሳሪያ በትምህርት ቤት አውቶብስ ላይ ፣ በትምህርት ቤት ንብረት ግቢ ፣ ወይም በትምህርት ቤት ኋላፊነት በሚካሄድ እንቅስቃሴ ውስጥ መያዝ፣

7. በቨርጅኒያ ሕግ አንቀድ § 18.2-83 መሰረት በትምህርት ቤት ሰራተኛ ወይም ከትምህርት ቤት አውቶብስ ወይም በትምህርት ቤት ንብረት ጋር የተያያዘ ቦንብ ማስፈራረት ወይም በውሸት ቦንብ ማስፈራራት፣

8. የት/ቤት አውቶብስ ላይ፣ በትምህርት ቤት ንብረት ግቢ፣ ወይም በትምህርት ቤት ኋላፊነት በሚካሄድ እንቅስቃሴ ውስጥ ማንኛውም ተማሪ እንዲያዝ ከተደረገ የቀረበበትን ክስ ጭምር እና፣

9. ማንኛውንም ህገ ወጥ የመሳሪያ፣ አልኮል፣ ድራግ ወይም የሲጋራ ምርቶች መያዝ፣

B. የዋና ሥራ አስኪያጁ (ሱፐር ኤንቴንደንት) እና ርእሰ መምህሩ ወይም ርእሰ መምህሩ ተወካይ በአካባቢው ያሉ የሕግ አስከባሪ አካላት ሪፖርት የሚደረጉ ጥፋቶችን መቼም በሚፈፅሙበት ጊዜ በትምህርት ቤት የተመዘገቡ ተማሪዎች ጥፋት በአዋቂ ቢፈፀም ፌሎኒ ከፍተኛ ወንጀል ሊሆን እስከቻለ ወይም የድራግ ቁጥጥር ህግ በቨርጅኒያ ሕግ አንቀድ § 54.1-3400 የሚተላለፍ ከሆነ እና በት/ቤት አውቶብስ ላይ፣ በትምህርት ቤት ንብረት ግቢ፣ ወይም በትምህርት ቤት ኋላፊነት በሚካሄድ እንቅስቃሴ ውስጥ ወይም በአዋቂ ቢፈፀም ሚስዲማነር በሚከተለው አንቀፅ በዚህ ፖሊሲ VIII.A ከ(1) እስከ (8) ድረስ የተገለፁትን ድርጊቶች እና ተማሪው ለእርሱ/ለእርሶ ወላጅ/አሳዳጊ እንዲወስዶቸው መደረጉን ወይም አለመደረጉን ወይም ከ18 ዓመት በላይ እድሜ ከሆነ ቦንድ ዋስትና አሲዞ የተለቀቀ ስለመሆኑ። የዋና ሥራ አስኪያጁ (ሱፐር ኤንቴንደንት) በአንቀፅ § 16.1-260 በንዑስ ክፍል G መሰረት በአዋቂ ቢፈፀም ወንጀል ሊሆን የሚችል ጥፋት አንድ ወጣት ፈፀሞል የሚውል ማስታወሻ ሲደርሰው ዋና ሥራ አስኪያጁ (ሱፐር ኤንቴንደንት) ይህን መረጃ ወጣቱ ትምህርት ለሚከታተልበት ትምህርት ቤት ርእሰ መምህር ማሳወቅ ይኖርበታል።

C. ርእሰ መምህር ወይም የርእሰ መምህር ተወካይ በዚህ ፖሊሲ ንዑስ ክፍል VIII.A (1-8) መሰረት ሪፖርት ሊደርጉ የተባሉትን ሁሉም ድርጊቶች ለዋና ሥራ አስኪያጁ (ሱፐር ኤንቴንደንት) ሪፖርት ያደርጋል። ዋና ሥራ አስኪያጁ (ሱፐር ኤንቴንደንት) እነዚህ ድርጊቶች ዓመታዊ ሪፖርት ለትምህርት ዲፖርትሜንት ያደርጋል።

እነዚህ ሪፖርቶች በሚያዘጋጁበት ወቅት ርእሰ መምህሩ ወይም የርእሰ መምህሩ ተወካይ የተፈፀመውን ጥፋት፣ እስር፣ ወይም በሕግ አስከባሪ አካላት የተመዘገቡ ክሶች እና በዚህ ፖሊሲ ንዑስ ክፍል VIII.B መሰረት ሪፖርት የሚደርግባቸውን በትክክል ማሳየት አለባቸው።

D. ርእሰ መምህር ወይም የርእሰ መምህር ተወካይ በዚህ ንዑስ ክፍል ሪፖርት ሊደርግባቸው የሚገቡ ድርጊቶችን ጉዳዮን በፈፀመው ተማሪ ላይ የዲሲፕሊን እርምጃ ቢወሰድንም ባይወሰድም ወይም የተወሰደው የዲሲፕሊን እርምጃ ዓይነት ቢለይም በድርጊቱ ተሳታፊ ለሆነው ለማንኛውም ተማሪ ወላጆች/ አሳዳጊ ማሳወቅ ይኖርበታል። የዚህ ዓይነቱ ማስታወቂያ ተማሪው ካደረገው ድርጊት ጋር የተያያዘ ብቻ መሆን አለበት እና የሌሎችን ተማሪዎች መረጃ መካተት አይኖርበትም።

E. በዚህ ንዑስ ክፍል ሪፖርት ሊደረግ የሚችል ድርጊት አንድ ተማሪ በሚፈፀምበት ወቅት በዋና ሥራ አስኪያጁ (ሱፐር ኤንቴንደንት) ተገቢነቱ ከታመነበት ይህ ተማሪ እንዲህ ዓይነት ድርጊት እንዳይፈፀም ለመከላከል፣ ጣልቃ ለመግባት በተዘጋጀ ፕሮግራም ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆን ሊጠየቅ ይችላል።

F. በፌደራል ሕግ፣ ደንብ ወይም ህግጋት በሌላ አባባል ካልተገለፀ በስተቀር ርእሰ መምህሩ ማንኛውንም ድርጊት በዚህ ፖሊሲ ንዑስ ክፍልVIII.A ከ(2) እስከ (7) በዝርዝር የተጠቀሱትን ድርጊቶች እንደወንጀል ሊታዩ የሚችሉ ጥፋቶችን ወዲያውኑ ለሕግ አስከባሪ አካላት ሪፖርት እና በዚህ ፖሊሲ ንዑስ ክፍልVIII.A ክፍል (1) የተገለፀውን ድርጊት ለአካባቢው ለሕግ አስከባሪ አካላት ሪፖርት ሊያደርግ ይችላል።

በተጨማሪም በፌደራል ሕግ፣ ደንብ ወይም ህግጋት በሌላ አባባል ካልተገለፀ በስተቀር ርእሰ መምህሩ ማንኛውንም ድርጊት በዚህ ፖሊሲ ንዑስ ክፍልVIII.A ከ(2) እስከ (5) በዝርዝር የተጠቀሱትን ድርጊቶች እድሜው ባልደረሰ ተማሪ ላይ ጥፋት የተፈፀመበት ወላጅ/ አሳዳጊ ጥፋቶችን ወዲያውኑ ለሕግ አስከባሪ አካላት ሪፖርት ማድረግ ይኖርበታል። ከዚህ በተጨማሪ ሕጉ በሚጠይቀው መሰረት ርእሰ መምህሩ ለአካባቢው የሕግ አስከባሪ አካላት ሪፖርት ስላደረገው ወላጅ/ አሳዳጊ የአካባቢውን ሕግ አስከባሪ አካላት ለተጨማሪ መረጃ ማግኘት ይችላሉ የሚፈልጉ ከሆነ።

G. ለዚህ ክፍል አገልግሎት “ወላጅ” ወይም “ወላጆች” ማለት ማንኛውም ወላጅ ወይም ሌላ ሰው ልጁን የመቆጣጠር ሃላፊነት ያለበት ሰው ማለት ነው።

## IX. የታገደ እና /ወይም የተባረረ ተማሪዋችን መልሶ ማስገባት

ከኤሲፒኤስ ት/ቤት ያተገደ ማንኛውም ተማሪ በአስተዳዳሩ ስር ባሉ ሌሎች ትምህርት ቤቶች ገብቶ ለመማር ብቁ አይደለም እርሱ/እርሶ ወደ መደበኛ ትምህርት ቤቱ ለመመልስ ብቁ እስካልሆነ ድረስ።

ከሰላሣ (30) ቀናት በላይ በትምህርት ቤት ቦርድ ወይም በቨርጂኒያ ስቴት የሚገኝ የግል ትምህርት ቤት ከትምህርት የታገደ ወይም በሌላ ስቴት ወይም በቨርጂኒያ የተባረረ ወይም በሌላ ስቴት ባለ የግል ትምህርት ቤት እንዳይመዘገብ የተከለከለ ማንኛውም ተማሪ በፖሊሲ JEC መሰረት በአሌክሳንደሪያ ከተማ የሕዝብ ት/ቤቶች እንዳይገባ ሊታገድ ይችላል። ከሰላሣ (30) ቀናት በላይ ከትምህርት የታገደ ከሆነ ከትምህርት የሚገለልበት ጊዜ መጠን ከታገደበት ቀናት መብለጥ አይኖርበትም። የዚህ ዓይነት የተባረረ ተማሪ ትምህርት እንዳይከታተል እንዲገለል በሚደረግበት ወቅት የትምህርት ቤት ቦርድ በቨርጂኒያ ህግ § 22.1-277.06 መሰረት ያባረረው የትምህርት ቤት ቦርድ ተማሪው ወደ ትምህርት መልሶ ለመከታታል ያስቀመጠውን ሁኔታ ይህ የትምህርት ቤት ቦርድ እንዳለ ሊቀበለው ወይም በከፊል ወይም ሁሉንም ሁኔታ ሊቀይረው ይችላል። የአሌክሳንደሪያ ከተማ ትምህርት ቤት ቦርድ ወደ ትምህርት ለመመለስ ሌላ ተጨማሪ ቅደም ሁኔታ አያስቀምጥም።

የትምህርት ቤቱ ርእሰ መምህር ወይም የእርሱ/የእርሶ ተወካይ ያለ ወላጅ ውይይት ተማሪውን መልሶ ማስገባት ተገቢ ነው ብለው እስካላመኑ ድረስ ማንኛውም የታገደ ተማሪ ወደ መደበኛ የትምህርት ፕሮግራም በቀጥታ ሊገባ አይችልም የዚህ ዓይነቱ ተማሪ እና ወላጆች/አሳዳጊዎች ስለተማሪው ባህሪ መሻሻል ከትምህርት ቤት ሃላፊዎች ጋር ካልተወያዩ።

ይህን ፖሊሲ ወይም የJEC ፖሊሲ የትምህርት ቤት አጀማመር ፖሊሲ ወላጅ/ አሳዳጊ ማክበር ካልቻለ የትምህርት ቤቱ ቦርድ የወጣት ወይም የቤት ውስጥ ግንኙነት ፍርድ ቤት የተማሪውን ባህሪ ለማሻሻል በሚደረገው ጥረት ሆን ተብሎ ያለአግባብ ተሳታፊ አለመሆን በመግለፅ በወላጅ/አሳዳጊ ላይ ተገቢውን እርምጃ እንዲወስድ ሊጠይቅ ይችላል።

የማባረር ሁኔታ የማግለሉ ጊዜ እንደተጠናቀቀ ወይም ምዝገባውን በመያዝ ይህም በትምህርት ቤት ቦርዱ፣ በዋና ሥራ አስኪያጁ (ሱፐር ኤንቴንደንት) ወይም ተወካዩ የሚወሰን ይሆናል እንደጉዳዮ ዓይነት አቤቱታው በሚሰማበት ጊዜ ሊወሰን ይችላል ተማሪው ለትምህርት ቤት ቦርዱ ወደ ትምህርት ቤት ለመመለስ ሌላ ማመልከቻ ሊያቀርብ ይችላል ወደ ትምህርት ቤት ለመመለስ የቀረበው ሌላ ማመልከቻ ተቀባይነት ካላገኘ የትምህርት ቤት ቦርድ ቀጣይ አገዳው ጊዜ መጠን ይገልፃል እና በቀጠይ መልሶ ለማመልከት የሚችልበትን ጊዜ ያሳውቃል። **የተባረረ ተማሪ ወደትምህርት ለመመለስ የሚያመለክትበትን ወይም በድጋሚ የሚያመለክትበትን ጊዜ GD-R/JGE-R ደንብ የአሰራር ሂደቱን እና የጊዜ ሰሌዳውን ይዘረዝራል።**

የትምህርት ቦርድ በዚህ ንዕስ ክፍል መሰረት የታገዱ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ቦርዱ የተዘጋጀ አማራጭ የትምህርት ፕሮግራም በእገዳው ጊዜ እንዲከታተሉ ሊፈቅድ ይችላል።

## X. የአካል ጉዳት ያላቸው ተማሪዎች ዲሲፕሊን መቅጣት

ኤሲፒኤስ የአካል ጉዳት ያላቸው ተማሪዎች ትምህርት ሕግ (IDEA) እና የ1973 የመልሶ ማቋቋሚያ ሕግ ክፍል 504 የአካል ጉዳት ያላቸው ተማሪዎች የዲስፕሊን ቅጣት በተማሪዎች የባህሪ ህግጋት እና የJGDA ፖሊሲ የተገለፁትን ይከተላል።

የፀደቀው፤ ሴፕቴምበር 5፣ 1996
የተሻሻለው፤ ጁላይ 10፣ 1997
የተሻሻለው፤ ጁን 18፣ 1998
የተሻሻለው፤ ጁላይ 12፣ 2001
የተሻሻለው፤ ጁላይ 1፣ 2005
የተሻሻለው፤ ጁን 15፣ 2006
የተሻሻለው፤ ዲሴምበር 19፣ 2013
የተሻሻለው፤ ዲሴምበር 18፣ 2014
የተሻሻለው፤ ጁን 11፣ 2015
የተሻሻለው፤ አክቶበር 25፣ 2018

የሕግ ማጣቅሻ 20 U.S.C. § 7151.

የቨርጂኒያ ሕግ፣ 1950, እንደተሻሻሉት አንቀፃች §§ 15.2-915.4, 16.1-260, 18.2-119,18.2-308.1, 18.2-308.7, 18.2-308.8.2:2, 22.1-200.1, 22.1-254, 22.1-276.01, 22.1-276.2, 22.1-277, 22.1-277.04, 22.1-277.05, 22.1-277.06, 22.1-277.07, 22.1-277.07:1, 22.1-277.08, 22.1-277.2, 22.1-277.2:1, 22.1-279.3:1.

(8)VAC -560-10

የቃላት መፍቻ፤

| | |
|---|---|
| GBEB | በትምህርት ቤት የሰራተኛ መሳሪያ |
| IGBH | አማራጭ የትምህርት ፕሮግራሞች |
| JEC | የትምህርት ቤት ምዝገባ መጀመር |
| JFC | የተማሪ ባህሪ |
| JFC-R | የተማሪ ባህሪ መመዘኛ ደረጃ |
| JFCD | በትምህርት ቤት መሳሪያዎች |
| JGD-R/JGE-R | የተማሪ እገዳ/መባረር ሕጎች |
| JGDA | የአካል ጉዳይ ያለው ተማሪ ዲሲፕሊን ቅጣት |

JGDB የአካል ጉዳይ ያለው ተማሪ ዲሲፕሊን ቅጣት ካባድ የአካል ጉዳይ በማድረስ